በግሬን የተዘጋጀ | ሐምሌ 2 2012 (መስፈንጠሪያ፡ Corporations)

# የአፍሪካ ሴቶች እና ነጻ የንግድ ቀጠናዎች ምንና ምን ናቸው?

## የአፍሪካ አሕጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና ሲፈተሽ



አንዲት ኡጋንዳዊት ወጣት ሴት፣ በካምፓላ ዋንዴጌያ ገበያ መንገድ ዳር ምግብ (ድንች ቺፕስ) እያዘጋጀች
ፎቶ፡ ኖርበርት ፔትሮ ካሉሌ

**በቅርቡ የፀደቀው የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) በአሕጉሩ ረብቧል፡፡ ይህ በአፍሪካ ኅብረት መሪነት ሊተገበር የታቀደ ግዙፍ ነጻ ገበያ አፍሪካን በገበያ ማስተሳሰር፣ በሀገራቱ መካከል ንግድን ማሳደግ፣ እና ቀጠናዊ ውሕደትን ማበረታታትና ማጠናከርን ግብ አድርጓል፡፡ ዕቅዱን በበጎ የሚመለከቱ አስተያየት ሰጪዎች አፍሪካን በኢኮኖሚ የሚያጎለብት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይህ ጽሑፍ ግን ጉዳዩን በአሕጉሩ የግብርና ሥራ ቁልፍ ሚና ካላቸው ከሴቶች ሁለንተናዊ ሕይወት ጋር በማያያዝ ተጽዕኖውን ይሞግታል፡፡ በርግጥ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ለአፍሪካ ሴቶች ምን ዕድል፣ ምን ዕዳ ይዟል? በምግብ ምርትና ንግድ ሚናቸውስ ላይ ተጽዕኖው ምንድነው?**

## ነጻ የንግድ ስምምነቶች ለአፍሪካ እንግዳ አይደሉም

የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ከፍ ባለ ደረጃና በስፋት መተግበሩ ካልተለየ በስተቀር ባለፉት ጥቂት ዐሥርት ዓመታት በአሕጉሩ ከተተገበሩ የንግድ ስምምነቶች ጋር ተመሳሳይ ግቦች ያሉት ነው፡፡ ወጣም ወረደ፤ ከዚህ ቀደም የተለዩ አሕጉራዊ ቀጠናዎች ላይ በግድና በዘዴ የተጫኑ በዝባዥ የንግድና ኢንቨስትመንት ስምምነቶችና አሠራሮችን በአሕጉር ደረጃ ለመተግበር የተነደፈ የኮርፖሬት የንግድ አጀንዳ ማስፈጸሚያ ነው፡፡

እአአ በ2000 ዓ.ም. አሜሪካ ከሰሐራ በታች ያሉ ሀገራት ምርቶቻቸውን ከቀረጥ፣ ታሪፍና ኮታ ነጻ ወደ አሜሪካ ገበያ እንዲያስገቡ የሚያስችላቸውን ‹‹አፍሪካ ግሮውዝ ኤንድ ኦፖርቹኒቲ አክት›› አጎዋ የተሰኘ የተናጠል ፖሊሲ አጽደቃ ተግባር ላይ አዋለች፡፡ ይህ ከቀረጥ፣ ታሪፍና ኮታ ነጻ የገበያ ፈቃድ ጨርቃ ጨርቅ፣ አልባሳት፣ ጫማ፣ የምግብ ምርቶችና አበባን ጨምሮ ከ6000 በላይ ምርቶችን ያካተተ ነው፡፡ በዚህም የተወሰኑ የአፍሪካ ሀገራት በአሜሪካ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው የዕድሉ ተጠቃሚ ለመሆን ችለዋል፡፡ (የግርግ ማጣቀሻ 1ን ይመልከቱ፡ አጎዋ ተጠቃሚነት መመዘኛ መስፈርት)

የሆነ ሆኖ፤ አጎዋ ከሀያ ዓመታት በኋላም እዚህ ግባ የሚባል ወጤት አላስገኘም፡፡ እስካሁን በአጎዋ ሙሉ ተጠቃሚ የሆኑት ሦስት ሀገራት ብቻ እነርሱም አንጎላ፣ ደቡብ አፍሪካና ናይጄሪያ ናቸው፡፡ በአጎዋ ወደ አሜሪካ የሚደረገው የወጪ ንግድ እአአ በ2011 ዓ.ም. ከነበረበት 68.2 ቢሊዮን ዶላር እአአ በ2014 ዓ.ም. ወደ 23.2 ቢሊዮን ዶላር አሽቆልቁሏል፡፡ (የግርግ ማጣቀሻ 2) የትራምፕ መንግሥት ይህንን አበረታች ያልሆነ ውጤት ከመፈተሽ ይልቅ አዲስ የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶችን ከሰሐራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት ጋር መፈጸም በመቀጠል በኬንያ ጀምረዋል፡፡ ዘርፉን ያጠኑ ባለሙያዎች እንደሚመሰክሩት፤ ይህ የዩኤስ-ኬንያ የንግድ ውል አብነት ያደረገው በኢፍትሐዊነቱ የሚኮነነውንና አወዛጋቢ የሆነው የዩኤስ-ሞሮኮ የንግድ ውል ነው፡፡

አውሮፓን በተመለከተ፤ የአፍሪካ፣ ካሪቢያንና ፓስፊክ ሀገራት ከቅኝ ግዛት ነጻ መውጣታቸውን ተከትሎ ጥምረት በመፍጠር ከአውሮፓ ኅብረት ጋር የተለያዩ የንግድ ስምምነቶችን ሲዋዋሉ ቆይተዋል፡፡ ከተጠቃሾቹ ቀዳሚው የያውንዴ ዲክላሬሽን ሲሆን ተከትሎም የሎሜ ኮንቬንሽን I-IV እና የኮቶኑ ፓርትነርሺፕ አግሪመንት ይገኙበታል፡፡ ይህም ሆኖ ለሙሉ ትግበራ የበቁት ውሱን የሽግግር ስምምነቶች ብቻ ናቸው፡፡

ስዊዘርላንድ፣ ኖርዌይ፣ አይስላንድና ሊሽተንስታይን የተጣመሩበት የአውሮፓ የነጻ ገበያ ማኅበር [The European Free Trade Association (EFTA)] በአፍሪካ አጋር ሀገራትን በመፍጠር የራሱን ነጻ የንግድ ቀጠና እየመሠረተ ይገኛል፡፡ ይህም ቢሆን የተቀዳው ከምዕራባውያኑ ኃያል ሀገራት የነጻ ንገድ ቀጠና መርሆችና ውሎች ነው፡፡



ኡጋንዳ፤ ግዌሪ ክፍለ-ከተማ፤ ሶሮቲ ቀበሌ፡ ታዳጊ ልጃገረድ አትክልት በመልክ በመልክ ትለያለች
ፎቶ፡ ኖርበርት ፔትሮ ካሉሌ

በሌላ ወገን፤ ጃፓንና ቻይና እስካሁን ከአፍሪካ ጋር ይህ ነው የሚባል የንግድ ስምምነት አልፈጸሙም፡፡ ነገር ግን የኢንቨስትመንት ማበረታቻና እና የእርዳታ ስምምነቶችን ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራትና ከፍለ-አሕጉራዊ አደረጃጀቶች ጋር ማድረጋቸው አልቀረም፡፡

የአፍሪካ ሀገራት ርስ በርሳቸው የሚያደርጉት መደበኛ ንግድ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ በተለይ ባለፉት ዐሥርት ዓመታት አጠቃላይ የሀገራቱ የወጪና ገቢ ንግድ ድርሻው ሁለት በመቶ ብቻ ነው፡፡ የአፍሪካ አሕጉራዊ የነጻ ገበያ ቀጠና እቀርፈዋለሁ የሚለውም ይህንኑ ችግር ነው፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 3)

## ሴቶችና ንግድ በአፍሪካ፡ የእስካሁን ውጤቶች

ሀገርአቀፍም ይሁን ድንበር ተሻጋሪ የአፍሪካ ንግድ በዋናነት ኢ-መደበኛ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ የተጠና የቁጥር ማጣቀሻ ባይኖርም በግርድፉ ከ30-40 በመቶ እንደሚሸፍን ይገመታል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 4) እስከ 40 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ኢ-መደበኛ በሆነው የንግድ ዘርፍ በተሰማራባቸው እንደ ደቡብ አፍሪካ ባሉ ሀገራት 70 በመቶ ግብይት የሚከናወነው በምግብ ዘርፍ ነው፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 5) ይህ ሁኔታ በመላ አሕጉሩ ተመሳሳይ ሲሆን የንግድ እንቅስቃሴ ትልቁ ድርሻ የምግብና የግብርና ምርቶች ነው፡፡ በዚህ ውስጥ የሴቶች ድርሻ ከፍተኛ ሲሆን በተለይ በገጠር እርሻ የጉልበት ሥራ 60 በመቶ እንዲሁም በምግብ ምርትና ዝግጅት 80 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ (ሳጥን 1ን ይመልከቱ፡ ሴቶች በአፍሪካ ግብርና)

## ሳጥን 1: ሴቶች በአፍሪካ ግብርና

በእርሻ ሥራ የሴቶች ሚና እንደ ሰብሉ ዓይነት፣ የምርት ዑደት፣ ዕድሜና ጎሣ/ብሔረሰቡ ቢለያይም ማረምና ምርት መሰብሰብ ባመዛኙ የሴቶች ተግባራት ናቸው፡፡ ይህ ክፍያ የማያስገኙላቸውን ምግብ የማዘጋጀት፣ ማገዶ የመሰብሰብ፣ ውኃ የመቅዳትና መሰል የቤት ውስጥ ኃላፊነቶቻቸውንም ይጨምራል፡፡ በገጠር የጉልበት ሥራ መስክ ያላቸው ተሳትፎ እንደየአካባቢው ቢለያይም አሁንም ድረስ ብዙኀን ሴቶች ያለክፍያ የሚሠሩ፣ ሥራቸውም በወቅቶች የሚወሰንና የትርፍ ጊዜ ነው፡፡ ለተመሳሳይ ሥራም ከወንዶች ያነሰ ይከፈላቸዋል፡፡ የንግድ ዘርፎችን በተመለከተ ሴቶች በአመዛኙ በፍራፍሬ፣ አትክልትና አበባ ምርት ወጪ ንግድ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡

GRAIN | THE SUMODE FOUNDATION | Seed Savers Network Kenya

በዘርፉ ያላቸው ድርሻ በመሠረታዊነት ሰብል ማምረት፣ የቤት እንስሳትን መንከባከብ፣ ምግብ ማዘጋጀትና ማብሰል፣ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪና በመሰል የገጠር ኢንተርፕራይዞች ተቀጥሮ መሥራት፣ ማገዶ መልቀምና ውኃ መቅዳት፣ ጥቃቅን የንግድ ሥራ፣ ቤተሰብና ቤት ማስተዳደርን ይጨምራል፡፡ ሌላው ዐቢይ የአፍሪካ ሴቶች ሚና የሰብልና ዕጽዋት ዘሮች ጠባቂነታቸው ነው፡፡ በአብዛኛው የአፍሪካ ማኅበረሰቦች የሰብልና ዕጽዋት ዘሮችን የመምረጥ፣ የማዘጋጀትና የማቆየት ተግባራትን የሚከውኑት ሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ተግባራት በመንግሥታት ትርፍ የሚያስገኙ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ተደርገው ባይታዩም ለገጠር ሕይወት እጅግ ቁልፍ መሆናቸው እሙን ነው፡፡

የቀደሙ ነጻ የንገድ ቀጠና ስምምነቶች፣ በትግበራ ሂደትም ጭምር የሴቶችን ጥቅሞች፣ ፍላጎቶችና ስጋቶች በመመለስና በማስከበር በኩል መልካም ስም የላቸውም፡፡ እንዳውም፤ ከአፍሪካ ውጪ ባሉ ቀጠናዎች የነጻ ገበያ ንግድና ኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችና ውሎች ላይ የሚሰነዘሩ የሴታውያን [feminists] ትችቶች ስጋቶቹ ከአፍሪካ ሁኔታ ጋር በእጅጉ የተቀራረቡ መሆናቸውን የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ ይህን በተመለከተ ዋነኞቹ የሙግት ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡-

በመሠረታዊነት የነጻ የንግድ ቀጠና ውሎች በቀጥታ ከሴቶች የመብት ትግል ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ውሎቹ የወጪ ንግድን አዋጭ ለማድረግ ሀብት ለማፍራት የሰው ኃይልን እንደ ርካሽ ግብዓት መጠቀምን ስለሚያበረታቱ ነው፡፡ ከዚህ የሰው ኃይል ውስጥ ይከፈላቸውም አይከፈላቸውም ትልቁን ቁጥር የሚይዙት ሴቶች ናቸው፡፡ እአአ በ1993 ዓ.ም. በአሜሪካ፣ ካናዳና ሜክሲኮ መካከል የሰሜን አሜሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት ከተፈረመበትና ተከትሎም እአአ በ1995 ዓ.ም. በዓለም የንግድ ድርጅት ምስረታ የንግድና የኢንቨስትመንት ውሎች ኢፍትሐዊ የኢኮኖሚ ሞዴሎችንና ደረጃዎችን በሌሎች የዓለም ክፍሎች በማስፋፋት የጥቂቶች ፍላጎትና ጥቅም ማስከበሪያ፣ ብዙኀንን ማስገበሪያ በመሆን በዓለማችን የጾታ፣ የመደብ እና የዘር ኢ-ዕኩልነት እንዲንሰራፋ መሣሪያ ሆነዋል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 8)

በአዕምሮአዊ የፈጠራ መብት ከለላ የሰብልና ዕጽዋት ዘሮች የግል ንብረትነት ስለሚመዘገቡ ሴቶች ለእርሻ ተግባር የሚውሉ ግብአት እንዳያገኙ ያግዳቸዋል። በተጨማሪም፤ የዘላቂ ግብርና የጀርባ አጥንት የሆነውን ዘር የማቆየት፣ የመለዋወጥና የመሞከር ተፈጥሮአዊ መብታቸውን ይነጥቃቸዋል፡፡ እንደ አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ግብጽ፣ ቱኒዚያና ደቡብ አፍሪካ ያሉ ሀገራት ከአሜሪካ፣ ከአውሮፓ ኅብረትና ከአውሮፓ የነጻ ገበያ ንግድ ማኅበር ጋር በገቧቸው የንግድ ውሎች አስገዳጅነት ለዓለ ማቀፉ አዳዲስ ሰብሎችና እጽዋት ዝርያዎች ጥበቃ ማኅበር [International Union for the Protection of New Varieties of Plants (UPOV)] ሕጎችና አሠራሮች እንዲገዙ ተደርገዋል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 9) የማኅበሩ ሕግጋት በተፈጥሮ መብቶች ላይ እገዳዎችን የሚጥል ከመሆኑም በላይ ወደፊት ድቅል ዝርያዎችን ሙሉ በሙሉ የግለሰቦችና ድርጅቶች የግል ንብረት ለማድረግ በር ከፋች መሆኑ አይካድም፡፡ እዚህ ላይ ሴቶች በሰብልና ዕጽዋት ዘር ማቆየት ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ልብ ማለት ያሻል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 10) ይህን ሚና ከተቀሙ ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚናቸውና ከውሳኔ ሰጪነት መገፋታቸው በዚያም ዐቅማቸው መሸርሸሩ አይቀርም፡፡

የመድኃኒት አቅርቦት ሌላኛው የስጋት ምንጭ ሲሆን በንግድ ውሎች ውስጥ በሚካተቱ የእእምሮአዊ ንብረት ሕጎች ምክንያት አሳሳቢ እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ ለአብነት ያህል ደቡብ አፍሪካ በሁለትዮሽ የነጻ የንግድ ውሎችም ይሁን በዓለም የንግድ ድርጅት ማዕቀፍ ውስጥ የመድኃኒት ፓተንት ፕሮቪዥኖችን አተገባበር በመሞገትና በማሸነፍ የቆየ መልካም ስም አላት፡፡ የዚህም ትሩፋት ለአሕጉሩም ጭምር ነው፡፡ በተለይ አሁን እንደ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በገጠመን ወቅት ይህን ትግልና ውጤት ማስጠበቅና ማስቀጠል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 11)

የአገልግሎት ሊበራላይዜሽን ውኃን ወደ ግል ሀብትነት ቀስበቀስ ሲያዛውር የውኃ አቅርቦት መቀነስ እንደሚከተል እሙን ነው፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፤ ይህ በተለይ በኢኮኖሚ ዐቅማቸው ደካማ በሆኑ ማኅበረሰቦች ውስጥ በሌሊት ረጅም መንገድ በመሄድ ውኃ መቅዳት ኃላፊነት ላለባቸው ሴቶች ሌላ ትልቅ ጫና የሚፈጥር ነው፡፡ እንደ ታንዛኒያ፣ ጋናና ደቡብ አፍሪካ ያሉ ሀገራት የዓለም የንግድ ድርጅትና ዓለማቀፉ የገንዘብ ድርጅት የብድር ፖሊሲዎች ባመጡት ጣጣ ምክንያት የዚህ መከራ ገፈት ቀማሽ ከሆኑ ሀገራት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በአንጻሩ የአውሮፓ ሀገራት በቀጣይ የኢኮኖሚክ ፓርትነርሺፕ አግሪመንት ውይይቶች በውኃ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶቻቸው ሰፊ መብቶችንና የውዝግብ መፍቻ ልዩ አሠራርን ለማጎናጸፍ ይደራደራሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች የነጻ ገበያ የንግድና ኢንቨስትመንት ውሎች በሚሰጡዋቸው የተለዩ የማበረታቻ ፕሮቪዥኖች ምክንያት የሴቶችን ጨምሮ የብዝበዛ ዓይነተኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የኢኮኖሚ ዞኖች በሀገራዊ የሥራና ሠራተኛ ወይም በአካባቢ ጥበቃ ሕግጋት ስለማይገዙ በዝቅተኛ ምንዳ፣ በጎስቋላ መኖሪያ፣ በንጽሕና ጉድለት የሚታወቁ ስመ-ጥፉ የሥራ ከባቢዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ የሴቶችን መከራ የሚያበዙ ክፉ ልማዶች መብቀያ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በርከት ያሉ የአፍሪካ ሀገራት ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና የኢንቨስትመንት ኮሪደሮች ያላቸው ሲሆን መሬትና መሰል ሀብቶችን በሚመለከቱ ሀገራዊ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች አይገዙም አለያም የተለየ መብት ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሴቶች ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጫና ማሳደሩ እሙን ነው፡፡ (የግርግ ማጣቀሻ 12) እነዚህ ኢ-ፍትሐዊ አሠራሮች የአፍሪካ ነጻ የንገድ ገበያን ጨምሮ ወደፊት በሚመጡ የነጻ ገበያ የንግድ ስምምነቶች ሕጋዊ ከለላ እያገኙ መሆኑ እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡

በኢንቨስትመንት ማበረታቻ የነጻ ገበያ የንግድ ሕጎች የጎለ

በቱና ከለላ የሚሰጣቸው በሰፋፊ እርሻ እና ግብርና ምርት ላይ የተሰማሩ ግዙፍ ድርጅቶች ገበሬዎችን ከመሬታቸው በማፈናቀል በምትኩ ዘላቂ ያልሆነ አመራረት ላይ የተመሠረተ የምግብ ምርት ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡ እንደ ኔስሊ (Nestle) እና ዳነን (Danone) ያሉ ግዙፍ የምግብ ንግድ ድርጅቶች በአፍሪካ ገበያ መንቀሳቀስ ከጀመሩ የሰነበተ ሲሆን የወተትና ወተት ተዋጽኦ፣ የቡና እና ተቀነባብረው የታሸጉ ምግቦች ለውስጥም ለውጪም ንግድ በስፋት ያቀርባሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ እንደ ናይቫሳ (ኬንያ) እና ሾፕራይት (ደቡብ አፍሪካ) ያሉሱ ፐርማርኬቶች ከምዕራቡ ዓለም የሸርክና ኢንቨስትመንትን በመሳብ ለባለቤቶቻቸው ዳጎስ ያለ ትርፍ ያስገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል እንደ ኬረፎር (Carrefour) እና ኦቻን (Auchan) ያሉ ግዙፍ የችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች የአፍሪካን ገበያ ለመቀራመት መግባት ጀምረዋል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 13) የሴቶች ሕይወት በሚመሠረትባቸው - በአፈር፣ በብዝኃ-ሕይወት፣ ውኃና መሰል የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ሳያንስ እንደ ያራ (Yara)፣ ዜኔንታ (Syngenta)፣ ባየር (Bayer) ያሉ ማዳበሪያና የሰብል ኬሚካል አምራቾችም የአፍሪካ ገበሬዎችን ከመበዝበዝ አልቦዘኑም፡፡ ይህ ሰፋፊ እርሻ አሠራርን የማስፋፋት ፍላጎት በአፍሪካ ከቅኝ ግዛት ዘመን ጀምሮ ሲሠራበት የቆየ ሲሆን ለሴቶች መከራ እንጂ መልካም ዕድል እንዳልያዘ ሐቅ ነው፡፡ የሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት የሥራ ዕድል ይፈጥራል የሚል ሙግት ቢኖርም ዕድሉ ግን እዚህ ግባ የማይባል ደመወዝ የሚከፍል፣ ሴቶች በአካባያቸው ያለን ሀብት፣ ንጹሕ ውኃና የጤና አገልግሎት እንዳይጠቀሙ የሚያቅብ፣ ሲብስም የጥቃት ሰለባ የሚያደርጋቸው መሆኑ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 14) ዓለማችንን እየናጠ በሚገኘው በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የዓለም የምግብ ድርጅት ዐሥር ሀገራት (ግማሾቹ ከአፍሪካ) በምጽአታዊ ረኃብ ይመታሉ ብሎ ቢተነብይም የምግብ ምርቶች ከምሥራቅ አፍሪቃ በራሰልስን ጨምሮ ሱፐርማርኬቶቻቸው ወደተራቆቱት የአውሮፓ ከተሞች በአየር ሲጓጓዙ ለመታዘብ በቅተናል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 15)

ኮቪድ-19 ቀድሞም ቢሆን ኢ-መደበኛ ነጋዴዎችን ለማሳደድ ሰበብ ይፈልጉ ለነበሩት ከሰሐራ በታች ያሉ መንግሥታት መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል፡፡ በኢ-መደበኛ ንግድ የተሰማሩ ሴቶች ለቤተሰቦቻቸውና ለማኅበረሰባቸው መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች መሆናቸው ይታወቃል፡፡

ለማጠቃለል፣ በአፍሪካ የነጻ ገበያና የኢንቨስትመንት ውሎች፣ በሴቶችና በጦረኝነት መስፋፋት መካከል ያለውን ትስስር ጠንቅቆ መረዳት ይኖርብናል፡፡ የትራምፕ አስተዳደር በቀጠናው የአሜሪካ ዋነኛ የጸረ-ሽብር አጋር ለሆነችው ኬንያ የመጀመሪያውን የአፍሪካ ነጻ ገበያ "ዕድል" መስጠቱ በአጋጣሚ ነው ብሎ መጠየቅ ያሻል። (የግርጌ ማጣቀሻ 16)

## የአፍሪካ ነጻ ገበያ የንግድ ቀጠና ከሌሎቹ ይሻል ይሆን?

የአፍሪካ ነጻ ገበያ ቀጠና እንደ ነጻ ንግድ ስምምነት የጸደቀው እአአ በሜይ 30 2019 ዓ.ም. ቢሆንም በቀጠናው ነጻ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲጀመር የተቀረጠው እአአ በጁን 1 2020 ዓ.ም. ነበር፡፡ ድርድሩ ግን እስካሁን እንደቀጠለ ነው፡፡ የታሪፍ ድንጋጌዎች ስምምነት ላይ ካልተደረሰባቸው ጉዳዮች ውስጥ ሲሆኑ አገልግሎቶችን በተመለከተ የአዕምሯዊ ንብረት መብቶችና ኢንቨስትመንት እአአ ለ2020 ዓ.ም. ይክረም የተባሉ አጀንዳዎች ናቸው፡፡

የአፍሪካ ነጻ ገበያ ቀጠና በሂደት ላይ ያለ እንጂ ዝርዝር ድንጋጌዎቹና አፈጻጸማቸው ስምምነት ተደርሶባቸው ገና አልጸደቀም፡፡ ይሁንና እስካሁን እንደታዩት ነጻ የንግድ ቀጠናዎች የአፍሪካን ንግድና ኢንቨስትመንት ሊበራላይዝ ለማድረግ የሚያስችል መላ ይዞ ይመጣል በሚል ከፍተኛ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ አተገባበሩ፣ ለምሳሌ ታሪፍን በተመለከተ እንደየሀገራቱ ዐቅም የሚወሰን ሆኖ ነገር ግን ሁሉንም የሚያስተሳስር ሥርዓት ይኖረዋል፡፡ የአውሮፓ ኅበረት የአፍሪካ ነጻ ገበያ ቀጠና ወደ ተግባር እንደገባ ከቀጠናዊ ወይም ክፍለ-አሕጉራዊ መዋቅሮች ጋር ስለመደራደር እያሰበ ይገኛል፡፡

55 በመቶ የአፍሪካን የሰው ኃይል የሚይዘውና ትልቁ የሴቶች ቀጣሪ የሆነው ግብርናና የምግብ ምርት በአፍሪካ ነጻ ገበያ ቀጠና ዐይን ከተጣለባቸው ዘርፎች አንዱ ነው፡፡ የሀገራት ድንበሮች እንዲከፈቱ የሚፈለገውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ይህም ገና ስምምነት ባልተደረገባቸው የቁስ በቁስ የታሪፍ አሠራሮች መሠረት ሸቀጦችን ወደ ገበያዎች በገፍ ለማስገባት ያስችላል፡፡ በአፍሪካ ነጻ ገበያ ቀጠና ከዚህ ቀደም በምሥራቅ አፍሪካ የጋራ ገበያ የተግበራ ፕሮቶኮል እንደታየው ብዙ ሴቶች ለማይገኙበት ለከፍተኛ ሙያተኞች ብቻ ዕድል የሚሰጥ ይሆናል ተብሎ ቢፈራም በአንጻሩ ያልተገደበ ድንበር-ዘለል የሠራተኞች ፍሰት እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል የሚልም ተስፋ አለ፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 17) በሌላ በኩል፣ የእሕልና እጽዋት ዘሮች የፈጠራ መብቶችን ከዓለማቀፉ ያዳዲስ ሰብሎችና እጽዋት ዝርያዎች ጥበቃ ማኅበር አሠራሮች [International Union for the Protection of New Varieties of Plants (UPOV)] ጋር በማስማማት ማዋሐዱ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡

በአብላጫው የአፍሪካ ክፍል ድንበር ተሻጋሪ ንግድ የሚከውኑት ሴቶች ናቸው፡፡ የንግድ ዘርፎቹም ጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ የግብርና ምርቶችና የፍጆታ ቁሳቁስ ሲሆኑ የንግድ እንቅስቃሴውንም በግለሰብ ደረጃ በየሳምንቱ ይከውናሉ፡፡ ድንበር ዘለል ንግዱ በትንሽ መጠንና ቶሎ ቶሎ የሚደረግ በመሆኑ ከትርፉ ኪሳራው ይበልጣል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 18) የንግድ ሕግጋትንና መመሪያዎችን አለማወቅና ተገቢ የገበያ መረጃ አለማግኘት ጉዳዩን የበለጠ ያከብድባቸዋል፣ ለአካላዊና የጾታ ጥቃትም ያጋልጣቸዋል፡፡ (የግርጌ ማጣቀሻ 19) የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና የግዙፍ የንግድ ድርጅቶችን ፍላጎት ዋና ግቡ ያደረገ በመሆኑ የነዚህን ሴቶች ችግር ጉዳዩ ይላል ብሎ መጠበቅ የዋኅነት ይሆናል፡፡

በሴቶች ላይ ተጽዕኖ ያለው ሌላው የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና አካል ስፔሻል ኢኮኖሚክ አሬንጅመንትስ [Special Economic Arrangements] የተሰኘው ድልድል ነው፡፡ እንደተጠበቀው፣ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ሰነድ "ልማት ለማቀላጠፍ" በሚል ሰበብ ለተለዩ የመንግሥት አካላት ልዩ የኢኮኖሚ ሽርክናዎች ወይም ቀጠናዎች እንዲፈጥሩ የሚያስችል ልዩ ፕሮቪዥን ይሰጣል፡፡ ውጤቱን ጊዜ የሚበይን ቢሆንም እንዲህ ያለው አሠራር ከዚህ ቀደም በተተገበረባቸው የዓለም

ከፍሎች እንደታየው ለሴቶች መልካም ዕድል የያዘ አይደለም ለማለት ያስደፍራል፡፡

## ማሳረጊያ

ላለፉት ሦስት ዐሥርት ዓመታት በአፍሪካ የተተገበሩ የነጻ ገበያ ውሎችንና ተግዳሮቶቻቸውን በቅርበት የተመለከቱ ሁሉ ማንሳት የሚገባቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል፤ ውሎቹ ለማኅበረሰብ ዕድገት የሴቶችን ሚና አጎልብተዋል ወይ? ሴቶችን በኢኮኖሚ ዐቅም፣ በማኅበራዊ፣ ባሕላዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ አሳድገዋል ወይ? ለሴቶች ቤተሰባቸውን በአግባቡ የሚያስተዳድሩበት ተገቢ ሥራ አስገኝተዋል ወይ? የስነ-ተዋልዶ መብቶቻቸው ተከብረው በተሟላ ጤና እንዲኖሩ አስችለዋል ወይ? ዐለፍ ሲልም፤ እነዚህ የንግድ ውሎች ስድሳ በመቶ የሚሸፍነውን የአሕጉሩን መደበኛ ያልሆነ ገበያና የገበያ ትስስር ከመጋፋት ይልቅ ደግፈዋል ወይ? የሚሉት መሠረታዊ ናቸው፡፡

በርግጥ እነዚህ ውሎች ሴቶችን በተመለከተ መሠረታዊ ጥያቄዎች እንኳን መመለስ አልቻሉም፡፡ ቃል በተግባር ይለካል እንዲሉ የነጻ ገበያ ውሎች ከባዶ ተስፋ ውጪ በተጨባጭ ለሴቶችና ለሌሎች ግፉዓን ያስገኙላቸው ጥቅም የለም፡፡ ካጽናፍ እስካጽናፍ እየተተገበሩ ያሉትና የኒዮሊበራል አስተሳሰቦችን ማዕከል ያደረጉት እነዚህ የንግድ ውሎች የግዙፍ ኮርፖሬሽኖች ፍላጎቶች ማስፈጸሚያ ናቸው፡፡ በመሆኑም፤ ለአፍሪካውያን ፍላጎቶችና ተስፋዎች ዕውቅና የሚሰጡና ችግሮቻቸውን ከመሠረቱ የሚፈቱ አዳዲስ የንግድ ሥርዓቶች፤ በዘላቂ፣ ሁሉን-አካታች፣ ቅኝ-አገዛዛዊ እና ፓትርያርካዊ ያልሆኑ እሴቶች ላይ የቆሙ ስትራቴጂዎችን በምትክ መተለም ግድ ይላል፡፡



በኡጋንዳ ፖሊስ የአካባቢ ጥበቃ አሐድና ሠራዊቱ በቅንጅት የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመግታት የሕዝብ መጓጓዣን እና ከምግብና ምግብ-ነክ ውጪ ያሉ ገበያ ቦታዎችን የሚያግደውን የፕሬዚዳንቱን መመሪያ ሲያስፈጽሙ



የጎዳና ላይ ፍራፍሬ ነጋዴዎች በካምፓላ ኡጋንዳ በደንብ አስከባሪዎች ሲሳዳዱ ፎቶ፡ ባድሩ ካቱምባ / ኤኤፍፒ በጌቲ ኢሜጅስ በኩል

## Notes

1. Kennedy Senelwa, “East Africa exports to the US hit $1bn in the year to September 2018”, The East African, 31 December 2018, https://www.theeastafrican.co.ke/business/East-Africa-exports-to-the-US-hit--1bn-in-the-year-to-September/2560-4914404-12mqfte/index.html

2. Timothy Kalyegira, “What failure of AGOA says about Africans”, Daily Monitor, 24 May 2015, https://www.monitor.co.ug/OpEd/Commentary/failure-AGOA-Africans/689364-2727256-i5vcix/index.html

3. UNCTAD, June 2019: https://unctad.org/en/pages/PressRelease.aspx?OriginalVersionID=520

4. Joachim Jarrreau, et al. “Lifting the lid on the black box of informal trade in Africa,” The Conversation, September 2018: https://theconversation.com/lifting-the-lid-on-the-black-box-of-informal-trade-in-africa-102867

5. “Informal trade may hold the key to food security”, Fin24, 20 Oct 2018, https://www.fin24.com/Opinion/informal-trade-may-hold-the-key-to-food-security-20181017

6. GRAIN and AFSA, “The real seed producers”, 2018, https://grain.org/e/6035

7. A good summary from Latin America is provided by Graciela Rodríguez, “Impacts du libre-échange sur les femmes dans un monde globalisé”, in Alternatives sud, vol. 24, 2017, pp. 147-165. From Asia, please see the excellent materials from Asia-Pacific Forum on Women, Law and Development at https://apwld.org/tag/trade-liberalization/

8. See bilaterals.org website for many accounts, and particularly bilaterals.org, BIOTHAI and GRAIN, “Fighting FTAs”, 2008, https://www.bilaterals.org/fightingFTA-en-Hi.pdf

9. See GRAIN, “Trade agreements privatising biodiversity outside the WTO: 2018 update”, https://grain.org/e/6030. UPOV is a French acronym for Union for the Protection of New Plant Varieties, a type of patent regime for seeds.

10. See GRAIN and AFSA, “Th real seed producers”, 2019, https://grain.org/e/6035

11. AFTINET, “293 community Groups Call on World Trade Organization to stop other negotiations and focus on access to life-saving medical supplies”, 20 April 2020, http://aftinet.org.au/cms/node/1859

12. See for example Eric Toussaint et al., “South Africa’s Special Economic Zones in Global Context,” ACCEDE, September 2019: https://accede.co.za/wp-content/uploads/2019/09/ACCEDE%20&%20FES%20Policy%20Working%20Paper%20No.1_WEB.pdf

13. See GRAIN, “Supermarkets out of Africa! Food systems across the continent are doing just fine without them”, November 2018, https://grain.org/e/6042

14. See RADD, Muyissi Environnment, Culture Radio, Natural Resource Women Platform, GRAIN and WRM “Breaking the silence: Industrial oil palm and rubber plantations bring harassment, sexual violence and abuse against women,” March 2019: https://grain.org/e/6164

15. “Tanzania’s horticulture industry gets new lease of life”, The Citizen, 14 April 2020, https://www.thecitizen.co.tz/news/business/Horticulture-gets-new-lease-of-life/1840434-5523522-exursez/index.html

16. Claire Felter, “What would a US-Kenya trade deal mean?”, Council on Foreign Relations, 21 Feb 2020, https://www.cfr.org/in-brief/what-would-us-kenya-trade-deal-mean. From 2002-2017, US counterterrorism assistance spending in Africa was highest in Kenya ($9.2bn). See Stimson Study Group on Counterterrorism Spending, May 2018, https://www.stimson.org/wp-content/files/file-attachments/CT_Spending_Report_0.pdf

17. SEATINI Uganda, “Free movement of workers in the East African Community: Implications for youth employment in Uganda”, 2014, https://www.seatiniuganda.org/publications/research/35-free-movement-of-workers/file.html

18. EASSI, “Women informal cross border traders: Opportunities and challenges in the East African Community”, 2012, https://eassi.org/wp-content/uploads/2019/07/Women-Informal-Cross-Border-Traders-Opportunities-and-Challenges-in-the-EAC-Action-research-2012.pdf

19. United Nations Conference on Trade and Development, “Borderline: Women in informal cross-border trade in Malawi, the United Republic of Tanzania and Zambia”, 2019, https://unctad.org/en/PublicationsLibrary/ditc2018d3_en.pdf

GRAIN

THE SUHODE FOUNDATION

Seed Savers Network

Kenya